# <u>ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ናት</u>

*ከአስተዋይ በቀለ*

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራን ለሻቢያ ፎርፌ የሰጠ እንዳይመስላችሁ።

ወያኔ አሸንፎ ሳይሆን ሆን ተብሎ በተሸረበና በተቀነባበረ ፀረ-ኢትዮጵያ ኢንተርናሽናል ሴራ ለንደን ላይ ተሰይሞና በሳተላይታቸው ተደግፎ እየተመራ አዲስ አበባ እንደገባ ወዲያውኑ በአፍሪካ አዳራሽ ባዘጋጀው የሰኔ ኮንፈረንስ ላይ ነፍሳቸውን ይማርና ፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ ባደረጉት ንግግር ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንደሆነች አረጋግጠው እዚያው አዳራሹ ባልኮኒ ላይ ቁጭ ብሎ ይሰማ የነበረውን ኢሳያስ አፈወርቂን ናላው እስከሚዞር ድረስ ሃቁን አስገስተውና አስምረው ነገሩት።

እርሱም በብስጭትና በውርደት እየተቁነጠነጠ የማይተኙልን እንዳሉ እናውቃለን በማለት *ሥጋቱን* ሳይሸሽግ ገልጧል። ***እንቢ ለአገሬ ! እንቢ ለዳር ድንበሬ ! ብሎ ያልተኛለት የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነት ነው።***

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራን በሚመለከት ጥርትና ንቅንቅ የማይል አቋም አለው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ መላው የኤርትራ ምድር፣ በቀይ ባሕር ውስጥ ያሉ አሥራ ሦስት ደሴቶች፣ ባሕር ውስጥ ያሉ ሃብቶች፣ በሳዑዲ አረቢያና በየመን ትይዩ የሆነው ስትራቴጅክ የባሕር ጠርዝ የመርከብ መተላለፊያውና የአየር ክልሉ ወዘተ… ሁሉ የእናት አገር ኢትዮጵያ ምንጊዜም የማይገሰስ፣ የማይከፋፈልና የማይነጣጠል የግዛት አንድነት አካል ናቸው።

በዚህ የእናት አገር አካል ላይ ሕልውና ያለው ራሱን "ስቴት ኦፍ ኤርትራ" ወይም "ዳውላት ኤሪትሪያ" ብሎ የሚጠራ አገርና መንግሥት መኖሩን የኢትዮጵያ ህዝብ በዲፋክቶም ሆነ በሕግ አያውቅም።

አሁን በኤርትራ የኢትዮጵያ ምድር ላይ ያለው ሁኔታ በወያኔና በሻቢያ ሽርክናና ትግግዝ በማንአለብኝነት በጠበንጃ የተፈጠረ የአጋሚዶ ፕረሰንስ ወይም ሕላዌ ነው ብሎ ነው የሚያምነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራ ለጊዜው ለእናት አገር ኢትዮጵያ የሚቆረቆር ማዕከላዊ መንግሥት ባለመኖሩ እንደ ማፊያ ክልል ለጊዜው በሻቢያ አጋሚዶ ሥር ዋለች እንጂ ከኢትዮጵያ አልተገነጠለችም ብሎ ነው ጥርት ባለ አቋም ፀንቶ ያለው።

ብዙ አገሮች ደግሞ በኤርትራ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ፍላጎት ተነስቶ እንገነጠላለን ብሎ ሕጋዊ ፔቲሽን ፈርሞ አልጠየቀም፣ የወያኔ የሽግግር መንግሥት ተብዬውም ኤርትራን ለማስገንጠል የመላ-ኢትዮጵያ ሕዝብ ማንዴት አልነበረውም፣ በጠበንጃ አፈሙዝ የቀረበለትም የሪፈረንደም አማራጮች "ኢትዮጵያዊነት ወይም መገንጠልና ስቴት ኦፍ ኤርትራ መፍጠር" የሚሉ ስላልነበሩ በእነዚህ ድምር ምክንያቶች መንግሥታት ኤርትራን የኢትዮጵያ አካል ናት በማለት ሕጋዊ እውቅና ለሻቢያ አልሰጡም።

ጀርመኖችና የመኖች አገሮቻቸው ሁለት ላይ ተከፍለውባቸው-ዋናው ጀርመን የጂ.ዲ.አርን፣ የሰንዓ መንግሥት ደግሞ የአደንን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕልውናዎች ሳያውቁና ሳይቀበሉ ቆይተው በትግላቸውና በፅኑ የአገር ፍቅር አቋማቸው የየአገሮቻቸውን የግዛት አንድነት ሙሉ በሙሉ አረጋግጠዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብም የአጋሚዶ ኃይሎችን ደምስሶ የአገሩን የግዛት ሕልውና በአስተማማኝና በዘላቂነት ያረጋግጣል።